ጥምረት ለነጻነት ለእኩልነትና ለፍትህ በኢትዮጵያ

Alliance for Liberty, Equality and Justice in Ethiopia

# የጥምረት ለነጻነት ለእኩልነትና ለፍትህ በኢትዮጵያ

## Alliance for Liberty, Equality and Justice in Ethiopia (ALEJE)

## መመስረት አስመልክቶ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

ቀን ነሃሴ 10 2002 ዓ.ም

በኢትዮጵያ ውስጥ የተንሰራፋው የዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የስልጣን እድሜ መራዘም የሃገራችንን ብሄራዊ ጥቅምና ደህንነት የበለጠ የሚጎዳ ህዝብን የበለጠ ለስቃይና ለውርደት የሚዳርግ መሆኑን በመገንዘብና ይህንን አስከፊ ሂደት ማስቆም ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አለመሆኑን በመረዳት፣

የኢትዮጵያ ህዝብ፣ የራሱንና የሃገሩን ችግሮች የሚያወሳስበውን የወያኔ ዘረኛን አምባገነናዊ አገዛዝ በተናጠል የሚታገሉ ድርጅቶች አቅማቸውንና ጥረታቸውን አስተባብረው በግፍና መከራ አምራቹ አገዛዝ ላይ በጋራ እንዲነሱ ያለውን ጥብቅ ፍላጎት ግምት ውስጥ በማስገባት፣

የ 2002 የወያኔ ምርጫ ተውኔት የኢትዮጵያ ህዝብ በአንድ ዘረኛ፣ ፍጹም አምባገነናዊና አዋራጅ አገዛዝ ስር መውደቁን ከመቼውም በላይ ገሃድ ያደረገው መሆኑንና ይህንንም መከራና ውርደት ማስቆም የሚቻለው በተቀናጀ ህዝባዊ ሃይልና መራራ ትግል ዘረኛውና አምባገነናዊን አገዛዝ በሁሉም አቅጣጫና በሁሉም አይነት የትግል ስልት ወጥሮ በማንበርከክ ብቻ እንደሆነ በማመን፣

መሰረተ-ሰፊ የሆነና ሁሉን አቀፍ የአትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎችን ህብረት ምስረታ፣ ዘረኛውንና አምባገነናዊ የሆነውን የወያኔ አገዛዘ ማስወገጃ፣ ዘለቄታነት ያለው ሰላም ማስፈኛ፣ የሁሉም አይነት መብቶች፣ ነጻነቶችና የብሄራዊ አንድነትና ጥቅም ማስከበሪያ፣ የኢኮኖሚ እድገትና ማህበራዊ ፍትህ መቀዳጃ ፍቱን መሳሪያ መሆኑንም ከልብ በመቀበል፣

ይህ የሶስት ድርጅቶች የጥምረት ጅማሮ ወደ ሰፊና ሁሉን አቀፍ ህብረት የሚወስደን አንድ እርምጃ መሆኑን ከምር በማመን፣

ለሰፊና ሁሉን አቀፍ ህብረት ምስረታ ተግተን እንደምንሰራ ለህዝብ ቃል በመግባትና፣ ለዚህም አጣዳፊ የመተባበር ተግባር ሁሉም የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ታጋይ ሃይሎች ተግተው እንዲሰሩ ጥሪያችንን በማቅረብ:-

**ጥምረት ለነጻነት ለእኩልነትና ለፍትህ በኢትዮጵያ - Alliance for Liberty, Equality, and Justice in Ethiopia (ALEJE) ተብሎ የሚጠራውን ህብረት መመስረታችንን ለኢትዮጵያ ህዝብና ለወዳጆቹ ሁሉ እናበስራለን**።

1. የአፋር ሕዝብ ፓርቲ
2. ግንቦት 7 የነጻነት የፍትህና የእኩልነት ንቅናቄ
3. የኢትዮጵያ ሕዝብ የአንድነትና የፍትህ ንቅናቄ

ውድቀት ለዘረኛው አምባገነናዊ ስርአት!!!

ድል ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች በሙሉ!!!